መሪ ብርሃን

ለጽድቅ መንገድ
ከሞት ወደ ሕይወት

በዚህ መጽሐፍ የሚገኙት ታሪኮች በሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር ቀደም ሲል ከታተሙት መጻሕፍት በመ/ሮ ታዕ ኪዳን ዘለዓለም የተቀነባበሩ ናቸው።

ይህ የታሪክ ስብስብ በ1991 ዓ.ም. ታተመ።

አሳታሚ፦ መ. ኢ. የ‍ም. ድ. ሥ. ጽ. ክ.



ከብርሃነ ሕይወት መጻሕፍት

ማውጫ

አርእስት	ገጽ
መቅድም	
የወፍ ምሳሌ	4
የሰንሰለት ሠሪ መታሰር	5
የሰይጣን ባቄላ	6
የተረሳ ምስማር	8
መናደፊያ የለውም	11
አንበሳና መንገደኛ	14
ትልና እሳት	17
ዶሮና ጫጩቶችዋ	18
«በአንተ ፈንታ...»	19
ያጸደቀው ዳኛው ነው	22
ዕዳ የከፈለ ንጉሥ	24
ደም የተረጨ በር	25
«የኰሎኔል ቃል አይለወጥም»	28
ንጉሥ የማረው እስረኛ	31
ምነው ነቅተው ባመለጡ!	32
ክፈትለት!	34
«ዐሥር ሺህ ብር እሰጣለሁ»	35
«ከእነርሱ ጋር መግባት አችላለሁ»	36
የአንድ ሽማግሌ መንፈሳዊ ለውጥ	38
የእኔ ውሳኔ	

መቅድም

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም እያስተማረ በነበረበት ጊዜ ለተሰበሰቡት ሁሉ ጥልቅ የሆነው የሰማያዊ መንግሥቱ ትምህርት ይገባቸው ዘንድ ሊጥር ለገበረ በዘርና በእርሻ፥ ለነጋዴም በዕንቁ፥ ለሴት በቤትና በእርሾ በመሳሰለውና በሚያውቁት ተግባር በምሳሌ እያደረገ እንደገለጸላቸው ሁሉ፥ እንዲሁም ይህች መጽሐፍ በዚሁ መሠረት እንድትጠቅም ተጻፈች።

በዚች መጽሐፍ ከልዩ ልዩ መጻሕፍት የተሰባሰቡ ምሳሌዎችና የልዩ ልዩ ሰዎች ታሪክች ይገኛሉ። እነዚህም ምሳሌዎችና ታሪኮች ተየሰጪ ተግባርና የአሳቡ ዓላማ የሚያርፍባቸው ሲሆኑ፥ የእግዚአብሔር ፍቅር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ የተገለጸባቸው ናቸው።

አንባቢ ሆይ! ይህችን መጽሐፍ በምታነብበት ጊዜ ሁሉ፥ አንተ ራስህ ማን ወይም የትኛው መሆንህን ጠይቀህ ለማወቅ የምትችለው፥ አስቀድመህ ተግሳርህ ምን ዓይነት እንደሆነና የአሳብህ ዓላማ የት እንደሚደደርስህ ምን እንደሠራህ፥ ምን እንደሚያስፈልግህ በበኩልህ ስትረዳ ነው። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ስጦታ፥ ሰውም ሊያደርገው የሚገባው በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶና ተጽፎ እንዲገኝልህ ተዘጋጅተአልና የሚገባህን ነገር ለማድረግ ወዲያውኑ ቁርጠኛ ሁን።

በዚች መጽሐፍ የሚገኙት መንፈሳዊ ትምህርቶች በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ ናቸውና የተጠቀሱትን ክፍሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ አውጥተህ እያነበብህ ያዘሉትን ትምህርት እውነትነት ለራስህ ብታረጋግጥ የበለጠ ጥቅም ታገኝበታለህ።

ጥቅሶቹ በ1953 ዓ.ም. ታርሞ ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው። አልር አልርም ከታሪክ አተራረክ ጋር እንዲስማማ የጥቅሶችን ዋና ፍሬ ነገር በአጭሩ ስጥተናል።

የወፍ ምሳሌ



ከ1500 ዓመት በፊት የቅዱስ ወንጌል መልእክተኞች፥ ጣዖት ወደሚመለክበት ወደ አንድ ሩቅ አገር ሄዱ። ከዕለታት አንድ ቀን ምሽት ከእነዚህ መልእክተኞች አንዱ ወደ ቤተ መንግሥት ተጠርቶ ሄደ። ንጉሡም ከመኳንንቱና ከአገሩ አለቆች ጋር በታላቅ አዳራሽ ተቀምጦ ነበርና እንግዳውን፥ «አሁን ያመጣህልኝን አዲስ ትምህርት ንገረኝ» አለው።

ሰውዬውም እግዚአብሔር በራሱ መልክ የፈጠረውን ሰው ከኃጢአት ለማዳን ወዶ አንድያ ልጁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛ በመስጠት የዓለምን አሕዛብ ሁሉ ከጨለማና ከሞት ጥላ ውስጥ አውጥቶ ብርሃንንና የዘላለምን ሕይወት እንደሰጣቸው ለንጉሡ ነገረው።

ይህን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ንጉሡና መኳንንቱ የአገሩም አለቆች እርስ በርሳቸው መመካከር ጀመሩ። አንዳንዶቹ፥ «ነገሩ መልካም ነው» አሉ። ሌሎቹም፥ «መልካም አይደለም! ከጥንት የቆየን የአባቶቻችን ትምህርት ይበቃል» አሉ።

ከእነዚህ መካከል አንድ ሽማግሌ ተነሥቶ ንጉሡን እንዲህ ብሎ መከረው፦ «ግርማዊ ሆይ! እኛ በዚህ ተቀምጠን ስንነጋገር አንዲት ወፍ ከውጭ ከጨለማ ተነሥታ ብርሃን ወዳለበት ወደዚህ አዳራሽ ስትገባ አየኋት። ከገባችም በኋላ በአዳራሹ ውስጥ ጥቂት ደቂቃ ቆይታ እንደገና ወደ ጨለማ ወጥታ ተመልሳ ሄደች። እንዲሁም እኛ ያችን ወፍ በመምሰል

ለአጭር ጊዜ በዚህ ዓለም ስንመላለስ ሳለን ከወዴት እንደ መጣን፥ ከሞትንም በኋላ ወዴት እንደምንሄድ አናውቅም። ከአባቶቻችን ከሰማነው ትምህርት ይህን አልተማርንም። ዛሬ ግን በሰማነው ነገር እኛ ከወዴት እንደ መጣን፥ ወዴትም እንደምንሄድ ሰምተን ብርሃንን ተቀብለናል። ስለዚህ ይህን ትምህርት ልብ አድርገን መስማት ይገባናል።»

ንጉሡና አለቆቹም የሽማግሌውን ምክር ተቀብለው የወንጌል ብርሃን በአገራቸው እንዲበራና እንዲስፋፋ ፈቀዱ።

ይህ ታሪክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም።»[1] ሲል የተናገረውን ቃል ያሳስባል።

(1) ዮሐንስ 8፥12።

የሰንሰለት ሠሪ መታሰር

በዱሮ ዘመን አንድ ሰንሰለት የሚሠራ ሰው በግዞት ቤት እንደታሰረ ይነገራል። እርሱ ከእስራቱ ላምልጥ ብሎ የታሰረበትን እግር ብረት ለመስበር አስቦ ይመረምረው ጀመር። ነገር ግን ሲመረምረው እርሱ ራሱ በገዛ እጁ የሠራው እግር ብረት እንደነበረ ባየ ጊዜ በፍጹም ተስፋ ቈረጠ። ምክንያቱም እርሱ እኔ የምሠራውን ሰንሰለትና እግር ብረት ማንም ሊሰብረው አይችልም እያለ ጠንካራ ሰንሰለት በመሥራቱ ሁልጊዜ ይመካበት ስለ ነበረ ነው። አሁን ይህ ሰው እርሱ ራሱ በገዛ እጁ በሠራው ሰንሰለት ታሰረ።

እንደዚሁም ኃጢአት የሚሠራ ሰው ሁሉ እርሱ ራሱ በገዛ እጁ በሠራው የኃጢአት ሰንሰለት የታሰረ ነውና ማንም ሰው ይህን የኃጢአት ሰንሰለት ሊፈታ አይችልም። ኃጢአተኛውን ከእስራቱ የሚፈታው አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ሰንሰለትን ሁሉ ለመስበር የሚችል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በችግርህ አርሱን ፈልግ። እርሱም እንደሚል፦ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው።... እንግዲህ ልጁ አርነት (ነፃ) ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።»[1]

አንባቢ ሆይ! በዚህ የተሰፋ ቃል መሠረት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አንተንም ነፃ ቢያወጣህ በእውነት ነፃ ትወጣለህ።

(1) ዮሐንስ 8፥34፡36።

የሰይጣን ባቄላ

በምሳሌ ለማስረዳት የወደደ አንድ ሰባኪ እንዲህ ብሎ ተረከ፦

አንድ ቀን እጅግ ብዙ የሆነ አሳማ አንዱን ሰው ተከትሎ በመንገድ ሲጥመለመል አየሁ። የአሳማ መንጋ ከወደ ኋላ ሆኖ ሲነዱት እንኳ ግራና ቀኝ እያለ ነጂውን ያስቸግራል። በዚህ ጊዜ ግን ያላንዳች ችግር ተቀጣጥሎ ሰውየውን ተከትሎ ይሄድ ነበር። እኔም ሁኔታውን ለመረዳት ተከታትዬ ተመለከትሁ። ሰውየውም እየመራ ከብት ወደሚታረድበት ቄራ ሲደርስ በሩን ከፍቶ የተከተለውን የአሳማ መንጋ አስገባና መልሶ ዘጋ።

እኔም ወደ ሰውየው ቀርቤ፥ «ያላንዳች ችግር ይህን የሚያህል የአሳማ መንጋ ወደ ቄራው ውስጥ ልትመራው እንደምን ተቻለህ?» ብዬ ብጠይቀው ከት ብሎ ሳቀና፥ «በብብቴ የያዝሁትን አንድ ከረጢት ባቄላ አላየህም ይሆናል። ለአሳማዎቹ ደስ የሚያሰኛቸውን ነገር ባልሰጣቸው እንደሚያስቸግሩኝ አስቀድሚ አስተዋልሁ፤ ስለዚህ ከያዝሁት ባቄላ ሳንጠባጥብላቸው፥ ወደ መሞቻቸው ቦታ እንደሚደርሱ ሳያውቁ፥ ያንን እየለቃቀሙ ወደሚታረዱበት ቄራ ድንገት ገቡ! እንዳይወጡም ዘጋሁባቸው» አለኝ።

ሰባኪውም ይህን ያየውንና የሰማውን ከተረከ በኋላ ለአድማጮቹ፥ «እንደዚሁም ሰይጣን የምትወዱአቸውን ነገሮች ደጎና አድርጎ ያውቃልና እያንዳንዳችሁን እያታለለ በመንገዱ ባቄላውን እያንጠባጠበ ሲመራችሁ የመጨረሻውን ባቄላ የምትለቅሙበት ሰዓት ፈጥኖ ይመጣባችኋል፤ በዚያም ጊዜ የገሃነም ደጆች በስተኋላችሁ ይዘጋሉ» ብሎ አስረዳቸው።



ይህን ስብከት የሰማ አንድ ወጣት የዚህን ዓለም ሳቅና ጨዋታ ሀብቱንም በመከታተል የሰይጣንን ባቄላ እየለቃቀመ ወደ ጥፋት ከሚራመዱት አንዱ እርሱ ራሱ እንደነበረ አስተውሎ የሚድንበትን መንገድ ለመያዝ ይፈልግ ጀመር። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ድኖ ወደ ሕይወት በሚያደርሰው መንገድ ጌታችንን ለመከተል ከጀመረ በኋላ፥ «በፍጹም ሳልጠፋ እሄድበት በነበረው መንገድ ስላቆመኝ ስለዚያ ስብከት፥ እስከ ዘላለም ድረስ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ» ብሎ መሰከረ።

አንተስ በየትኛው መንገድ ትሄዳለህ? ባቄላውን እየለቀምህ ወደ ጥፋት በሚያደርሰው መንገድ ያን ታላቅ አታላይ ትከተለዋለህን? «መጨረሻቸው ጥፋት ነው፥ ሆዳቸው አምላካቸው ነው... አሳባቸው ምድራዊ ነው»[1] ከተባሉት ሰዎች ጋር ትሄዳለህን? «ፈቃዱን ለማድረግ በዲያብሎስ

ሕያዋን ሆነው።»[2] እንደተያዙ ታስተውላለህ? ወይስ ከወጥመዱ ወጥተህ ወደ ሕይወት በሚያደርሰው መንገድ ጌታችንን ትከተላለህ? ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር የታመነ መሪ የለም።

(1) ፊልጵስዩስ 3፥19፤ (2) 2 ጢሞቴዎስ 2፥25-26።

የተረሳ ምስማር

ከብዙ ዓመት በፊት አንድ ሰው ወደ አንድ መቃብር ቦታ ሄዶ ሲዘዋወር ሳለ አዲስ መቃብር የሚቈፍረውን ሰው አየና በአጠገቡ ቆሞ የሚቈፍረውን ቦታ ይመለከት ጀመር። ቈፋሪው ተግቶ ሲቈፍር ሳለ በድንገት ከአፈሩ ጋር አንድ የሰው ራስ ቅል አወጣ። በአጠገቡ ቆሞ ይመለከት የነበረው እንግዳ ሰውዬ ይህን የራስ ቅል አንሥቶ ሲመረምረው እውስጡ ሰንጥቆ የገባ አንድ ረጅም የዛገ ምስማር በማየቱ በጣም ደነገጠ። እርሱም አንዳች ሳይናገር በችኰላ ምስማሩን አውጥቶ በመሐረቡ ውስጥ ሸሽጎ ቈፋሪውን «ይህ የራስ ቅል የማን እንደሆነ ታውቃለህን?» ብሎ ጠየቀው።

ቈፋሪውም፥ «አዎን ሁልጊዜ ይሰክር የነበረ የአንድ ሱቅ ባለቤት የነበረ ይመስለኛል። ይህም ሰው በድንገት ሲሞት የአሟሟቱ ምክንያት በጭራሽ አልታወቀም» ብሎ መለሰለት።

እንግዳውም፥ «ሰውዬው ሚስት ነበረችውን?» ብሎ ጠየቀው።

ቈፋሪውም፥ «አዎን፥ ሰውዬው ከሞተ በኋላ ባለቤቲቱ በችኰላ ምንም ሳትዘገይ ሌላ ስላገባች ጕረቤቶችዋ ሁሉ ያሙአት ነበር። ታሪኩ ሁሉ ትዝ የሚለኝ በዚህ ምክንያት ነው» አለው።

እንግዳውም፥ «ሴቲቱ ገና በሕይወት አለችንን» ብሎ ጠየቀው።

ቈፋሪውም፥ «አዎን፥ ቤትዋም እንኳ እዚህ በአቅራቢያህ የምታየው ነው» አለው።

እንግዳውም ሰውዬ የሰማውን ሁሉ በልቡ እያወጣና እያወረደ መንገዱን ቀጠለ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ሴቲቱ ቤት ሄዶ ከእርስዋ ጋር መነጋገር ጀመረና ንግግራቸውን እንደ ቀጠሉ ስለ ሕግ ባልዋ እንድትነግረው እያስተዛዘነ ጠየቃት። እርስዋም ስለ ሕግ ባልዋ ስትነግረው በድንገተኛ ሞቱ እንዴት እጅግ አዝና እንደነበር መተረክ ጀመረች። ሰውዬው ይህን በሰማ ጊዜ መሐረቡን ፈታና ምስማሩን በድንገት ገልጦ በቍጣ ድምፅ፥ «አንቺ ሴት ይህን ምስማር አይተሽው ታውቂያለሽ?» ብሎ ጠየቃት። በዚህም ጊዜ ወዲያው ደንግጣ ፊትዋ በፍርሃት ተውጦ ሁለመናዋ ይንቀጠቀጥ ጀመር። ያንን የሚያስፈራውን ምስማር እያየች ለረጅም ጊዜ ዝም ብላ ከቈየች በኋላ በደልዋን ሁሉ ገልጣ ተናዘዘች።



ይህች ሴት የተንቀጠቀጠችው በምን ምክንያት ነበረ? ኃጢአትዋ እንደ ተገለጠባት የሚመስክረውን ምስማር በማየት ነው። ያን ምስማር በባልዋ ራስ ውስጥ ከመታች ብዙ ዓመት አልፎ ነበር። እርሱም ከተቀበረ በኋላ፥ «ግድ የለም፥ ሁሉ ደኅና ነው፤ ያደረግሁት ነገር ምንም አልታወቀብኝም» ብላ በማሰብ ደስ እያላት ትኖር ነበር። የሠራችውን ሥራ ያወቀባት ግንም አልነበረምና እንደ ገና ምስማሩን ከቶ የምታየው አልመሰላትም ነበር። ነገር ግን ከዕለታት አንድ ቀን ምስማሩ ከመቃብር ወጥቶ መሰከረባት።

አንባቢ ሆይ! ጊዜህ ከቀን ወደ ቀን እያለፈ ሲሄድ በልዩ ልዩ መንገድ ኃጢአት ትሠራለህ። ማንም አላየኝም ብለህ ስለምታስብ ኃጢአትህ የተደበቀ ይመስልሃል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዳየውና ኃጢአትህ ሁሉ እንደተመዘገበ አስታውስ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል፥ መተላለፌ በረታብኝ፤ ደግሞም፥ እኛን በሚቈጣጠር በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቈተና የተገለጠ ነው[1]። ኃጢአተኛ መሆንህን ታውቅ ይሆናል፤ ነገር ግን ኃጢአትህ ሁሉ እንደተጻፈና በፍርድ ቀን እንደሚያጋጥምህ አስበሃልን? ብዙ ጊዜ ኃጢአት ከሠራህ በኋላ በመጸለይ ወይም በመጾም ወይም ምጽዋት በመስጠት ከእግዚአብሔር ጋር ልትታረቅ ሞክረህ ይሆናል። ወይም ደግሞ፥ «እግዚአብሔር መሓሪ ነው» እያልህ ኃጢአትህን በጥልቅ መቃብር ውስጥ ልትቀብረው ሞክረህ ይሆናል። ነገር ግን ወዳጄ ሆይ፥ ያ የተደበቀው ኃጢአትህ ከመቃብሩ እንደሚወጣና እንደሚመሰክርብህ እወቅ። እስቲ ይህን ከባድ የሆነውን የጌታችንን ቃል አንብብ፦ «ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤»[2] ይህ ቃል ኃጢአትህን እንድታስብና ይቅርታን እንድትፈልግ ልብህን አውኮ ሕሊናህን ይውቀሰው። ብዙ ሰዎች፥ «እግዚአብሔር መሓሪ ነውና አይፈርድብንም» እያሉ ተስፋ ያደርጋሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ዓይኖች ክፉ እንዳያዩ ንጹሓን ናቸው[3]፥ በደለኛውንም እንዳልበደለ አይቈጥርም[4] ይላልና እግዚአብሔር በኃጢአት መፍረድ እንደሚገባው ያስተምረናል።

«እንግዲህ እግዚአብሔር መሓሪ አይደለምን?» ብለህ ብትጠይቅ፥ በእርግጥ እግዚአብሔር ባለ ብዙ ምሕረት እንደሆነ የሚታይበት የኃጢአተኞች ቤዛ እንዲሆን አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ በመስጠቱ ነው። በዚህ ሁሉ ምሕረቱን ብቻ ሳይሆን ቅን ፍርዱን ደግሞ እናያለን። እግዚአብሔር በምሕረቱ ለኃጢአታችን ማስተሰረያ ይሆን

ዘንድ ልጁን ላከልንና በቅን ፍርዱ ስለ እኛ ኃጢአት እርሱን ቀጣው። እንደተጻፈ፥ «እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ . እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።»[5]

ከዚህ ከጌታችን ሞት በስተቀር ሌላ ተስፋ የለህም። ኢየሱስ ክርስቶስ የግል መድኃኒትህ እንደሆነ ተረድተህ እርሱን በማመን ልትድን ትችላለህ እንጂ ሌላ የደኅንነት መንገድ ከቶ የለም። የዚያን የሚያስፈራውን «የምስማር» ምስክርነት ዝም ሊያሰኘው የሚችል፥ ለኃጢአተኞች የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ብቻ ነው። ምክንያቱም እርሱ ለአንተ የሚገባውን ቅጣት ተሸክሞ በእርሱ ከኃጢአትህ ሁሉ ትጸድቅ ዘንድ በአንተ ፈንታ የሞትን ፍርድ ተቀበለ።

አንባቢ ሆይ! ይህን ሁሉ ልብ አድርገህ አስብበትና ንስሓ ገብተህ በመድኃኒትህ በክርስቶስ አመን። ወደ እርሱም ቀርበህ፥ «ጌታ ሆይ! እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፤ ነገር ግን አንተ ስለ እኔ ብለህ የሞትህ መድኃኒቴና በድል አድራጊነት ከሙታን የተነሣህ ጌታዬ እንደሆንህ በፍጹም ልቤ አምኜ ከእንግዲህ ወዲህ ለአንተ እኖራለሁ» ብለህ አሳብህን ቈርጠህ ንገረው። ይህንም እንድታደርግ፥ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።»[6] የሚለው የሐዋርያው ዮሐንስ ቃል ይመራሃል።

(1) ዕብራውያን 4፥13፤ ዘኍልቍ 32፥23፤ (2) ማቴዎስ 12፥36፤
(3) ዕንባቆም 1፥13፤ (4) ዘጸአት 34፥7፤ (5) ኢሳይያስ 53፥5-6፤
(6) 1 ዮሐንስ 1፥8-9።

መናደፊያ የለውም

ከዕለታት አንድ ቀን ብዙ ሰዎች በአንድ ቦታ ተሰብስበው ከእባብ ጋር የሚጫወት አንድ ሰው ይመለከቱ ነበር። እባቡ



እጅግ የሚያስፈራ ተናዳፊ ዓይነት ነበረና ይመለከቱት የነበሩ ሰዎች በጣም ደንግጠው፥ ሰውዬው በድንገት ወድቆ ይሞት ይሆናል እያሉ ሲጠባበቁ ብዙ ጊዜ ቈዩ። ሰውዬውም በአንዳች ነገር እንዳልተጐዳ ባዩ ጊዜ፥ ይህ እንዴት ነው? እያሉ በመገረም እርስ በርሳቸው ይጠያየቁ ጀመር።

ሰውዬው ግን ያለ አንዳች ችግር ዝም ብሎ ቆሞ እባቡን በእጁ ይዞ እየተጫወተበት፥ በአንገቱና በክንዶቹ ዙሪያ እንዲዘዋወር ፈቀደለት።

ተመልካቾቹ እርስ በርሳቸው እየተጠያየቁ ልዩ ልዩ መልስ ሲሰጣጡ ሳለ በድንገት ከመካከላቸው አንድ ሰው ነገሩን አስተውሎ፥ «አሪ! እባቡ መናደፊያ የለውም» ብሎ ጮኸ። ይህ ሰው የተናገረው እውነት ነበረ። እባቡ ይናደፍበት የነበረው መርዛሙ መውጊያ ከአፉ ውስጥ ተነቅሎ ነበርና በዚህ ምክንያት ለመናደፍ በጭራሽ ስለማይችል፥ በፊት እጅግ ያስፈራ የነበረው እባብ ምንም የማይጐዳ ሆኖ ነበር።

እኛ በምን ምክንያት እባብ እንፈራለን? የሚጐዳበት መርዛም መናደፊያ ስላለው አይደለምን? ስለ ምንስ ሞትን እንፈራለን? ሞትን የምንፈራው እኮ፥ እንደ እባብ መናደፊያ ወይም መውጊያ ስላለው ነው፤ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚል፥ «የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው»[1]፥ ደግሞም፥ «ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ፥ ተመደበባቸው»[2] ይላል። እንግዲህ በኃጢአት ምክንያት ከቅዱሱ አምላካችን ፊት ለመቆም እናፍራለንና በዚህ

ምክንያት ሞትን እንፈራለን። እንደተጻፈ፥ «በጽዮን ያሉ ኃጢአተኞች ፈሩ፤ መንቀጥቀጥ ዝንጉዎቹን ያዘ፤ ከምትበላ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ? ለዘላለምም ከምትነድድ እሳት ጋር መኖርን የሚችል ከእኛ ማን አለ?»[3]...«አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና።»[4] ደግሞም እንደ ተጻፈ፥ «በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።»[5]

ከእባቡ ጋር ይጫወት የነበረ ሰውዬ የእባቡን መናደፊያ እንደ ነቀለ እንደዚሁም እኛ የሞትን መውጊያ ለማውጣት ብንችል ኖሮ ሞት ሊያስፈራን ባልቻለም ነበር። እንግዲህ የሞትን መውጊያ ሊያወጣልን የሚችል ማን ነው? እኛ ይህን ታላቅ ነገር ለማድረግ ኃይል የለንም፤ ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሞቱ ኃጢአታችንን አስወግዶ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የሞትን መውጊያ አውጥቶላቸዋልና ከእንግዲህ ወዲህ ሞት በምእመናን ላይ ሥልጣን የለውም፤ ሊጐዳቸውም ከቶ አይችልም። «ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ።»[6]

ንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ በሦስተኛው ዕለት አሳየኸን
በሞት ላይ ታላቁን ሥልጣንህን።
እጅግ በዛ ደስታችን፥ ተነሥቶአልና ጌታችን
ኀብራችንን ገብሮ፥ የሲኦልን ቁልፍ ሰብሮ
ላመን ትንሣኤህን፥ ላከህልን ብርሃንህን።

(1) 1ቆሮንቶስ 15፥56፤ (2) ዕብራውያን 9፥27፤
(3) ኢሳይያስ 33፥14፤ (4) ዕብራውያን 12፥29፤
(5) ዕብራውያን 10፥31፤ (6) 1ቆሮንቶስ 15፥55-57፡ 54፤

አንበሳና መንገደኛ

ከአያሌ ዓመታት በፊት አንድ ሰው ገንዘብ አገኛለሁ ብሎ ከአገሩ ተነሥቶ ሥራ ወደሚገኝበት ወደ ሌላ አገር ሄደ። ይህም ሰው በሄደበት አገር ብዙ ጊዜ ከሠራ በኋላ እንደገና ወደ አገሩ ለመመለስ አስቦ ገንዘቡን ይሰበስብ ጀመር። የተወሰነውም ቀን ሲደርስ ጓዙ ሁሉ የተከተተበትን ሳጥን ተሸክሞ መንገዱን ቀጠለ።



ይህም ሁሉ ሲሆን እርሱ በደስታ ወደ አገሩ ለመድረስ ተስፋ ነበረው እንጂ በመንገዱ የሚገጥመውን አደጋና ጭንቅ ምንም አላሰበም ነበርና በእጁ ከአንድ ዱላ በስተቀር አንዳች መሣሪያ አልነበረውም። እንደዚሁም ደግሞ የሚያጽናና ወይም የሚያበረታታ ጓደኛ አንድ ስንኳ አልነበረውም።

ብዙውን አገር አልፎ ከሄደ በኋላ ደንና ጫካ ወደ በዛበት፥ የአውሬ እንጂ የሰው ድምፅ ወደማይሰማበት ቦታ ደረሰ። በዚህ ጫካ ውስጥ ብቻውን ሲሄድ ቦታው አስፈሪ ከመሆኑ የተነሣ ልቡ በብዙ ሥጋትና ሽብር ተሞልቶ ነበር። ዳሩ ግን ዋና የፍርሃቱና የጭንቀቱ ጊዜ ገና ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

በዚሁ ጫካ ውስጥ ብዙ የሚያስደነግጡ ልዩ ልዩ አውሬዎች ነበሩበት፤ ከእነዚህም ሁሉ በላይ በግርማው እጅግ የሚያስፈራ ካገኘም የማይለቅ አንበሳ ነበረ። ሰውዬውም በድንገት ከአንድ ትልቅ አንበሳ ጋር ፊት ለፊት ተያይቶ እንደ ቆመ ባየ ጊዜ

እጅግ ይንቀጠቀጥ ጀመር። ደግሞም ወዲያና ወዲህ እየዞረ ቢመለከት ግንም ረዳት እንደማያገኝ፥ ሮጦም ለማምለጥ እንደማይችል ተረድቶ የያዘውን ሸክም አውርዶ ምናልባት አንበሳው ሸሽቶ ይሄድልኛል በማለት ዱላውን ይዞ እየደነፋ መሬቱን ይመታ ጀመር።

አንበሳው ግን ሰውዬውን በመናቅ የእርሱን ዱላና ድንፋታ ከምንም አልቈጠረውምና የሚያደርገውን ነገር እየተመለከተ ዝም ብሎ ቆመ እንጂ ከቦታው ምንም አልተንቀሳቀሰም። ሰውዬውም በዚህ ሁሉ ሕይወቱን ለማዳን ባልቻለ ጊዜ ጠፍቼአለሁ፤ እበላለሁም ብሎ ተስፋ ቈረጠ። አንበሳው ደግሞ እበላዋለሁ ብሎ ሲጠብቀው ቈየ።

አውን በሁለቱ መካከል አንድ ያልታሰበ ነገር ሊሆን ነው። አውሬ የሚያድን አንድ ሰው ጫካ ለጫካ ሲሄድ ውሎ አንበሳውና ሰውዬው ወዳሉበት አቅራቢያ ደረሰና፥ ቆሞ ሲያዳምጥ የሁለቱን ድምፅ ሰማ። ከዚህ በኋላ ጠመንጃውን አጉርሶ ቀስ እያለ ሄደና አጠገባቸው ሲደርስ የአንበሳውን ግንባር ተመልክቶ አንድ ጊዜ ቢለቅበት አንበሳው በመሞታት ሰውዬውም በመደንገጥ ሁለቱም በያሉበት ወደቁ። አዳኙም በሞት መካከል ወደ ነበረው ሰው ቀርቦ እፎኑን አንሥቶ «አይዞህ፥ ረድቼሃለሁ» ብሎ የገደለውን አንበሳና የረዳውን ሰው በመኪናው ጭኖ ቅርብ ወደ ነበረው ከተማ ደስ እያለው ሄደ።

እበላለሁ ብሎ ተስፋ በመቊረጥ ሕይወቱን ለሞት የሰጠ ሰውዬ ሳይሞት ቀረና፥ እበላለሁ ብሎ በደስታ ይፈነጭ የነበረው አንበሳ ሳያስበው ሞተ።

ይህ ታሪክ በእርግጥ ስለ መንፈሳዊ ነገር የሚገልጽ ነው። ሰው በራሱ ፈቃድና ያለ ረዳት በዚህ ዓለም ጫካ ሲመላለስ ሰይጣን እንደ አንበሳ ሆኖ ሊያጠፋው ይጠብቃል።

እንደተጻፈ፥ «ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤»[1]

ከሰውዬው ይልቅ አንበሳው እንደበረታና የአፉ ጉርሻ ሊያደርገው እንዳሰበ እንደዚሁ በእውነት ከእኛ ይልቅ ሰይጣን እጅግ ኃይለኛ ነውና ራሳችንን ለማዳን ከቶ አንችልም። በዚህ ምክንያት ብዙ ሰዎች በፍርሃት ባርነት ታስረው ለሰይጣን መሥዋዕትን እየሠዉ የጠንቋይንና የምዋርተኛን ምክር ይከተላሉ። ይህ ሁሉ ግን ያ ሰው በእጁ በያዘው በትር በከንቱ መሬቱን እንደመታው ዓይነት ይቈጠራል እንጂ የሚረዳ አይደለም።

ነገር ግን አንድ አዳኝ ሰው መጥቶ አንበሳውን አሸንፎ ሰውዬውን ከሞት አፋፍ እንዳዳነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰይጣንን ሥራ ሊሽር ከሰማይ ወርዶ ሰይጣንን ድል ነሥቶ ከጠላታችን እጅ አዳነን።[2] አሁን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሰው ሁሉ ከሰይጣን ባርነትና ከፍርሃት አርነት ይወጣል።

እንግዲህ ኀኖ ሰይጣንንና ርኩሳን መናፍስትን በመፍራት በልዩ ልዩም አምልኮና በጭንቀት የታሰርህ ሰው ሆይ! ለሰይጣን ሳይሆን ለእግዚአብሔር ለፈጣሪህ ታዝዘህ ሰይጣንን ባሸነፈ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመንና ዳን። በእርሱ ከዳኑት ሰዎች ሁሉ ጋር ደስ እያለህ እንዲህ ብለህ አመስግነው፦ «የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፥ ... የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል... በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን።»[3]

(1) 1 ጴጥሮስ 5፥8፤ (2) ዕብራውያን 2፥14፡15፤
(3) ሉቃስ 1፥68-75።

ትልና እሳት

ከኃጢአት ባርነት ነፃ የወጣ የክርስቶስንም ፍቅር የቀመሰ አንድ ሰው ነበረ። ይህም ሰው ከፍቅሩና ከደስታው ብዛት የተነሣ ሁልጊዜ ስለ መድኃኒቱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመናገር ይወድ ነበርና፥ ክርስቶስ ስላደረገለት ውለታ ሁሉ ቡብዙ በኩል እየመሰከረ ሲኖር አንድ የወንጌል ተቃዋሚ ሰው፥ «ሁልጊዜ ስለ ክርስቶስ የምትናገረው በምን ምክንያት ነው? ይህ ክርስቶስ ምን አደረገልህ?» ብሎ ጠየቀው።

ሰውዬውም በቃል ሳይመልስለት ጥቂት ቅጠልና ሣር ሰበሰበና በመሬት ላይ ክብ አድርጎ ከሠራ በኋላ አንድ ትል አነሣና በከበበው ሣር ውስጥ አስቀምጦ ቅጠሉንና ሣሩን በእሳት አያያዘው።

እሳቱም ሲነድ ትሉ ከሥቃይ ብዛት የተነሣ ብዙ ከተንፈራፈረ በኋላ ከእሳቱ ለማምለጥ ባለመቻሉ ተስፋ ቈርጦ ሞቱን በመጠባበቅ ተጠቅልሎ ተኛ።

በዚሁ ጊዜ ሰውዬው እጁን ዘረጋና ትሉን በጥንቃቄ እንሥቶ በደረቱ ላይ አስቀመጠው። ወደ ተቃዋሚውም ሰው ዘወር ብሎ «ይህን ትል አየኸውን?» ሲል ጠየቀው። «እኔ እንደዚህ እንደሚጠፋ ትል ነበርሁ፤ ያለ ተስፋ በኃጢአት ተይዤ ወደ ገሃነመ እሳት ቀርቤ ነበር። እጁን ዘርግቶ በጸጋውና በኃይሉ ከዘላለም ነበልባል ያዳነኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እኔ በኃጢአት የተሞላሁና የተከበብሁ ትል ስሆን በፍቅሩ በልቡ አጠገብ ያኖረኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በውኑ እኔ «ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ»[1] አይደለሁምን? የወደደኝና ስለ እኔ ራሱን የሰጠው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።[2] ሁልጊዜም ስለ እርሱ ለመናገር የምወድበት ምክንያት ይህ ነው።»

(1) ዘካርያስ 3፥2፤ (2) ገላትያ 2፥20።

ዶሮና ጫጩቶችዋ

ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ዶሮ በሣር መካከል እንቍላል ጣለች። ዐሥር እንቍላል እስኪሞላ ድረስ ሳታቋርጥ በየቀኑ ትጥል ነበር። ከዚያም በኋላ እንቍላልዋን እስከ ሦስት ሳምንት ድረስ ታቀፈችና በ21ኛው ቀን ዐሥር ጫጩቶችን ፈለፈለች።

ነገር ግን በሣር ውስጥ ዶሮና ጫጩቶች እንደነበሩ ያላወቀ ሰው ሣሩን አቃጠለው። እሳቱ በኃይል ነዶ እየተያያዘ ሲሄድ ዶሮዋ ደንግጣ ጫጩቶችዋን፥ ቁህ! ቁህ! ቁህ! ብላ ጠራቻቸው። እነርሱ ግን ትንንሾች ስለ ሆኑ ሸሽተው ሊያመልጡ አልቻሉም። እናታቸው ለብቻዋ አምልጣ ልትተዋቸው ሳታስብ ከክንፎችዋ በታች ሠውራ ታቀፈቻቸው። እሳቱ በላይዋ ላይ ካለፈ በኋላ እናትየዋ ተቃጥላ ሞታ ተገኘች። ጫጩቶችዋ ግን ድነው ተገኙ።



ያች ዶሮ ሕይወትዋን ስንኳ እስክትለውጥላቸው ድረስ ጫጩቶችዋን ወደደች። ይህም የእግዚአብሔር የአምላካችን ፍቅር ምሳሌ ነው! በመዝሙረ ዳዊት ተጽፎ እንደሚገኝ «በላባዎቹ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፤»[1]

እንደዚሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረ ጊዜ ሰዎችን ሁሉ ከጉዳትና ከጥፋት ለመጠበቅ ይወድ ነበርና ብዙዎች ወደ እርሱ መጥተው ሊታመኑበት እምቢ ባሉ ጊዜ፥ እርሱ በኀዘን ድምፅ፥ «ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ... ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ

ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም።»[2] አለ።

ፍቅሩ እጅግ ታላቅ ስለሆነ እኛን ሁላችንን ከሰይጣንና ከገሃነመ እሳት ለማዳን ብሎ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሕይወቱን ሰጠልን። ስለዚህ እኛ እምቢ ሳንለው ታምነንበት ወደ እርሱ እንጠጋ።

አምላኪ ሆይ! ስማ ጩኸቴን፤
ፈጥነህም አድምጥ ጸሎቴን።
ኀዘን ጸንቶብኛልና በክንፍህ ጥላ ሠውረኝ፤
ወደ ሕይወት አምባም ምራኝ።
ተስፋዬ ሆነሃልና በድንኳንህ እኖራለሁ፤
በክንፍችህም ጥላ እታመናለሁ።
ጌታ ሆይ! ክብርህ ይስፋ፥ ጸሎቴን ሰምተሃልና፤
መጠጊያም ሆነኸኛልና።
ሁልጊዜም ወዳንተ እግልዳለሁ፤
ለስምህም ዘላለም እዘምራለሁ።

(1) መዝሙር 90(91)፥4፤ (2) ማቴዎስ 23፥37።

«በአንተ ፈንታ ...»

በፈረንሳይ አገር አባቱና እናቱ ሞተውበት በሴት አያቱ ጥበቃ ያደገ አንድ ልጅ ነበረ። ይህም ልጅ ገና ሕፃን ሳለ ተደሳችና መልካም ተጫዋች ነበረ፥ ነገር ግን ክፉ የእጅ ዓመል ይኸውም ስርቆት ነበረበት።

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ሲመለስ ኪሶቹ እንደ ሰንጢ፥ እርሳስ፥ ኳሶችና ላጲስ በመሳሰሉ ልዩ ልዩ ነገሮች ተሞልተው አያቱ አየች። እርስዋም፥ «እኪስህ ውስጥ ጥቅጥቅ አድርገህ

የሞላሃቸውን ነገሮች አውጣ» ብላ አዘዘችው። ልጁም በትልቅ ድንጋጤ በኪሱ ውስጥ ያለውን አንድ በአንድ አወጣ።

«ይህን ሁሉ ከየት አመጣኸው?» ብትለው መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ። እንደገናም፥ «ከየት ነው ያገኘኸው? መልስልኝ!» አለችው። «የወሰድሁት ከተማሪዎች ጠረጴዛ ላይ ነው» አለ።

«እንግዲህ ልብ አድርገህ ስማኝ። ሁለተኛ በሰረቅኸው ገንዘብ ኪስህን እያጨቅህ እንዳትመጣ። ሹራብ የምሠራባቸውን ቀጫጭን ብረቶች ታውቃቸው የለምን? ዳግመኛ ብትሰርቅ ያንን ሹሉን ብረት እሳት እስኪመስል ድረስ አግዬ የስርቆት ልምድ ያለውን እጅህን እወጋዋለሁ። ዋ! ልብ አድርግ፤ ከቶ አልምርህም» ብላ በብርቱ አስጠነቀቀችው።

ልጁም ለትንሽ ጊዜ ጨዋ ሆነ፤ ነገር ግን እንደገና ወደ ጥንት ልማዱ ማለትም ወደ ስርቆት ተመልሶ ገባ። አያቱም አስቀድማ እንዳስጠነቀቀችው ተገቢ ቅጣቱን ልትሰጠው ተነሣች፤ ብረቱንም እሳት እስኪመስል ድረስ አግላ፥ «እጅህን ዘርጋ!» አለች። እርሱም እየተንቀጠቀጠ ዘረጋ።



ነገር ግን ከፍቅርዋ ብዛት የተነሣ ልብዋ ተጨነቀ፤ ቢሆንም የሌብነት ውጤት በዚህ ዓለምና ይልቁንም እግዚአብሔር ለሁሉ እንደ ሥራው በሚሰጥበት በፍርድ ቀን እንዴት እንደሚሆን ለማሳየት ብላ፥ «ልጄ ሆይ! ሌብነትህ አሳዛኝና አሳፋሪ፥ የረከሰና የተጠላ፥ የሚያመጣብህም ውጤት እጅግ በጣም የሚያስፈራ ነውና ቅጣቱ የሚገባህ ነው። ነገር ግን በአንተ ፈንታ እኔ

ልቃጠል» በማለት እጅዋን በእጁ ላይ አድርጋ እስኪኮማተርና እስኪጨስ እስኪያንገበግባትም ድረስ በጋለው ብረት የራስዋን እጅ አቃጠለች። ለልጅዋ የሚገባውንም ቅጣት እርስዋ ራስዋ ከተቀበለች በኋላ፥ «የሠራኸውን አስተዋልህን? በል ተገንዘበው» አለችው።

ያ ልጅም አያቱ ያደረገችለትን ከቶ አልረሳም። በዕድሜም ከጐለመሰ በኋላ፥ «ከዚያ ቀን ወዲህ መስረቅ ተውሁ፤ በደሌ ተወዳጅ አያቴን የቱን ያህል እንደ ጐዳት አስተዋልሁ። ስረቅ ስረቅ የሚል አሳብ ሲመጣብኝ አያቴ በዓይኔ ላይ ድቅን ስለምትልብኝ ላደርገው ያሰብሁትን እተው ጀመር። የኃጢአት ቍስል እንዲሽር ፍቅር አስፈላጊ መሆኑን በአያቴ ፍቅር አስተዋልሁ» አለ።

ያች አያት «በአንተ ፈንታ እኔ ልቀጣ» ያለችው ቃል ከሰው ፍቅር ሁሉ የበለጠውን ፍቅር ያሳስበናል። እስከ ሞትዋ ድረስ ያደረገችውን ሁልጊዜ የሚያሳስብ የፍቅር ምልክት ማለትም የቍስልዋ ጠባሳ በእጅዋ እንደታየ አይጠረጠርም። ነገር ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ የሚታየው ምልክት እንዴት እጅግ ከዚህ የበለጠውን ፍቅርና የበለጠውን ሥቃይ ያሳስበናል! እርሱ ከቶ ኃጢአትን የማያውቀው ስለ እኛ ብሎ በመስቀል ላይ በምስማር እንደተቸነከረና እንደሞተ ስናስብ የእግዚአብሔርን ልጅ እስከዚህ ኀፍረትና ሥቃይ ያደረሰውን ኃጢአታችንን እንድንጠላ፥ መድኃኒታችንን በሙሉ ልባችን እንድንወደው አያደርግምን? በልብህ ዓይን ጌታህ ስለ አንተ መከራን ሲቀበል ድቅን እስኪልብህ ድረስ የመስቀልን ታሪክ አንብበህ አስተውል።[1] ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደወደደውና ራሱን ስለ እርሱ የሰጠ መሆኑን[2] የተናገረው አሳብ አንተንም የሚመለከት ነውና ይህንን ቃል ለራስህ ተቀበልና ዳን።

(1) ኢሳይያስ 53፥5-6፤ ዮሐንስ 19፥17-30፤ (2) ገላትያ 2፥20።

ያጸደቀው ዳኛው ነው።



የሮም መንግሥት ከፍ ከፍ ባለችበት ዘመን ይኖር ስለነበረ ሰለ አንድ ዳኛ የሚከተለው ታሪክ ይነገራል።

ከዕለታት አንድ ቀን የዚህ ዳኛ ልጅ ወንጀል ሠራና ጥፋተኛ መሆኑ በማስረጃ ተረጋገጠ። ፍርዱንም ይቀበል ዘንድ የራሱ አባት ወደ ሚፈርድበት ፍርድ ቤት ተወሰደ።

ዳኛውም ቅንና የማያደላ እውነተኛም ስለነበረ፥ ወንጀሉን የሠራው የራሱ ልጅ እንደሆነ ሳያስመስል በማስረጃ ተረጋግጦ የቀረበለትን ወንጀል ከመረመረ በኋላ እንደ ሕጉ መሠረት፥ «ይህ አጥፊ ይሙት በቃ ይፈረድበት!» በማለት የፍርዱን ሐተታ አዘጋጀ።

በታላቅ ጉባኤም ፊት ቆሞ፥ «እኔ እንደ መንግሥታችን ሕግ መሠረት ለወንጀለኛው ፍርድ የምሰጥ ዳኛ ነኝና ይህን ወንጀል የሠራ መሞት አለበት ብዬ በሁላችሁ ፊት የፍርድ ቃሌን እወስናለሁ። ነገር ግን እኔ ፈራጅ ብቻ ሳልሆን ይህን ወንጀል የፈጸመው ልጅ አባት ነኝና በልጄ ፈንታ ቅጣቱን በራሴ ሕይወት እፈጽማለሁ፤ ወንጀለኛ የሆነው ልጄም ነፃ ይውጣ» ብሎ ሰለ ልጁ ሞተ።

ከዚህ በኋላ አጥፊ የሆነውን ልጅ ወደ ሌላ ዳኛ ቢወስዱት እንኳ የወንጀሉ ቅጣት እንደ ሕጋችን መሠረት ተከፍሎለታልና

በምንም ዓይነት ጥፋተኛ ነው ብለን እንድንፈርድበት የሚያዘን ሌላ ሕግ የለንም፤ ፍርዱ ተፈጽሞአል፤ ቅጣቱም ተከፍሎአል፤ ነፃነት ይገባዋል እያለ ዳኛው ነፃነት እንደሚሰጠው ጥርጥር የለውም።

እኛም በሕግ መሠረት ለማንም ሳያደላ፥ ማንንም ሳይፈራ፥ በእውነት የሚፈርድ ጻድቅና ቅን የሆነ ፈራጅ አለን፤ እርሱም እግዚአብሔር ነው። ከሕጉ ውጭ የሆነውን ልዩ ልዩ ዓይነት ኃጢአት ስለሠራንም በሕጉ መሠረት ሊፈርድብን አያመነታም። ጻድቅና እውነተኛ ፈራጅ ነውና ይፈርድብናል። ነገር ግን ፈራጅ ብቻ ሳይሆን በአባት ፍቅር የሚወደን ፈጣሪ በመሆኑ፥ በእኛ ፈንታ ሆኖ የበደላችንን ቅጣት እንዲከፍል፥ እግዚአብሔር ወልድ ራሱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፥ ሥጋችንን በመልበሱ እንደ እኛ ሰው ሆነና ስለ እኛ ኃጢአት ሞተ። እንደዚሁ በሕግ የተወሰነውን ቅጣት በእኛ ፈንታ ሆኖ ከፈለልን።

ክርስቶስ ያደረገው ሁሉ ለእኔ ነው የምንል ሁሉ፥ የበደላችን ቅጣት ተከፍሎአልና ሙሉ ነፃነት ተሰጥቶናል። ያ ንጹሕና ቅዱስ ዳኛ፥ እርሱም እግዚአብሔር፥ በሕግ የተፈረደውን ፍርድና የተከፈለውን ቅጣት ተመልክቶ ነፃነት ይሰጠናል። እኛም እንዲያጸድቀን ይህን ሁሉ ላደረገልን ምሰጋናችንን እያቀረብን የተገኘልንን ነፃነት በእምነት እንቀበል።

ይህ ታሪክ፥ «ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያስረዳል። ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቊጣው እንድናለን።»[1] «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና...።»[2] የሚሉትን ጥቅሶች ያሳስበናል።

(1) ሮሜ 5፥8-9፤ (2) 1 ጴጥሮስ 3፥18።

ዕዳ የከፈለ ንጉሥ

ተራ ሰው መስሎ ከአገሩ ሰዎች ጋር ለመቀላቀል የሚወድ አንድ ታላቅ ንጉሥ ነበረ። ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ወታደሮች ሰፈር ሄዶ ሲዘዋወር ሳለ በአንድ ድንኳን ውስጥ ራሱን በክንዱ ላይ ተንተርሶ እንቅልፍ የወሰደውን አንድ ወጣት ሻምበል አየ። በአጠገቡም አንድ ወረቀትና አንድ ሽጉጥ ነበረ።

ንጉሡም ወደ ድንኳኑ ውስጥ ገብቶ በወረቀት ላይ የተጻፈውን የዕዳ ሂሳብ ዝርዝር አነበበ። ከሂሳቡ በታች ይህን ያህል ትልቅ ዕዳ ለመክፈል ማን ይችላል? የሚል ጥያቄ ተጽፎ አየ። ንጉሡ ይህን አንብቦ ሰውዬው ዕዳውን ሁሉ ለመክፈል ባለመቻሉ ተስፋ ስለቈረጠ ራሱን ለመግደል እንዳሰበ በግስተዋሉ ብዕር ይዞ፥ ይህን ያህል ትልቅ ዕዳ ለመክፈል ማን ይችላል? ተብሎ ከተጻፈው ጥያቄ በታች ስሙን ፈርሞበት ሄደ።

ከጥቂት ሰዓት በኋላ ሻምበሉ ከእንቅልፉ ነቃና ራሱን ለመግደል አስቦ ሽጉጡን አነሣ። ነገር ግን ለመጨረሻ ጊዜ የዕዳው ሂሳብ የተዘረዘረበትን ወረቀት ተመልክቶ ከጥያቄው በታች አዲስ ጽሕፈት አየ። ይህ ምንድር ነው? ብሎ ሲያስብ



የንጉሡን ፈርማ አውቆ ሽጉጡን አኑሮ፥ «እኔ ተኝቼ ሳለሁ ለካ ንጉሤ መጥቶ ይህን ያህል ከባድ ዕዳ ለመክፈል ተሰፋ ሰጥቶ ሄዶአል!» ብሎ እጅግ ደስ አለው።


ግለዳ ከንጉሡ ዘንድ የተላከ አንድ መልእክተኛ ለዕዳው የሚከፈለውን ገንዘብ ይዞ መጣ። ከዚያ

በኋላ ሻምበሉ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በእንዴት ያለ ፍቅር ንጉሡን ያገለገለው ይመስላችኋል?

እኛ ያለብንን ትልቅ የኃጢአት ዕዳ ልንከፍለው ከቶ አንችልም። ነገር ግን፥ «ይህን ያህል ትልቅ ዕዳ ለመክፈል ማን ይችላል?» እያልን ስንጨነቅ እግዚአብሔር «ኢየሱስ» ብሎ ይመልስልናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ዕዳችንን ለመክፈል ብሎ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተልን። ስለዚህ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የኃጢአትን ይቅርታ ተቀብሎ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰላም አለው። በእርግጥ «ኃጢአታችሁ ስለ ስሙ ተሰርዮላችኋልና» የሚለው አምላካዊ ቃል ይፈጸምለታል።

(1) 1 ዮሐንስ 2፥12።

ደም የተረጨ በር



ከዕለታት አንድ ቀን በውበትዋና በሀብትዋ በታወቀች አንዲት ከተማ ላይ ጦርነት ተነሥቶ ወራሪዎቹ ሀብትዋን ለመውረስ ሲሉ ነዋሪዎቹን በሙሉ ለመጨረስ አሰቡ። በየቤቱ እየገቡ ሰውን ማረድ ጀመሩ። ጩኸቱና ዋይታው የከተማዋን ጸጥታ አደፈረሰው። አልሞት ባይ ተጋዳይ ነውና ምንም እንኳ ድልን ባይጐናጸፉም አንዳ ንዶች ለመከላከል ሳይሞክሩ አልቀሩም።

ይህ ሲሆን አንድ ሰው እመንገድ ዳር ተደብቆ ወታደሮቹ የሚያደርጉትን ይመለከት ነበር። በተለይ በአንድ ቤት ውስጥ የገቡት ወታደሮች ሰዎቹን ሁሉ ገድለው በሩን በኋላቸው ሲዘጉ ሳለ፥ ከእነርሱ አንዱ ጨርቅ እደም ውስጥ ነክሮ ደሙን እበሩ ላይ ሲረጭ አየ።

ሰውዬው ወዲያውኑ ወታደሮቹ እንዳያዩት ግራና ቀኝ እየተመለከተ እከተማዋ መካከል በአንድ ትልቅ ቤት ውስጥ ሞታቸውን ይጠባበቁ ወደ ነበሩት ጓደኞቹ እየሮጠ ሄደ። እዚያም እንደደረሰ፥ «አሁን ከጠላቶቻችን እንዴት ለመዳን እንደምንችል አውቃለሁ» አላቸው።

እነርሱም ዓይኖቻቸውን ትኩር አድርገው ወደ እርሱ በመመልከት «እንዴት ለመዳን እንችላለን?» አሉት።

ሰውዬው፥ «እረ፥ ቀስ በሉ እንዳይሰሙን! ደም ከየትም ፈልገን በበሩ ላይ መርጨት ነው፤ ከዚያም ወታደሮቹ ደሙን ሲያዩ ተገድለዋል ብለው ያልፋሉ» አላቸው።

ከጓደኞቹ አንዱ፥ «የዚህ የዚህማ እጓዳ የታሰረ ፍየል አለ እኮ፤ የእርሱ ደም አይሆንምን?» ብሎ ጠየቀው።

ሰውዬው፥ «እንግዲያውስ ፍየሉን ፍታና አምጣው፤ እንረደውም» አለው።

ፍየሉም ወዲያው እንደመጣ አርደው ደሙን በበሩ ላይ ከረጩ በኋላ፥ ቤቱን ዘግተው ያለ ምንም ሹክሹክታ ተቀመጡ። ወታደሮቹ በዚያ በኩል ሲያልፉ ደሙን አይተው ሌሎች ጓደኞቻቸው እዚህ ቤት ገብተው ሰዎቹን ገድለዋቸዋል በማለት አልፈው ሄዱ። እዚያም ቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎች በሙሉ ከሞት ዳኑ።

እነዚያ ጨካኞች ወታደሮች ነዋሪዎቹ በሙሉ አንድ እንኳ ሳይቀር እንደሞቱ አስበው ነበር፤ ዳሩ ግን በፍየል ደም ሰበብ ጥቂቶች ሰዎች መዳናቸውን ተገንዝበናል።

ይህ ለእኛ ትልቅ ምሳሌ ነው። በዚህ ዓለም የምንኖር ሰዎች ሁሉ እያንዳንዳችን ሞት፥ ይኸውም ዘለዓለማዊ የገሃነም ፍርድ ተፈርዶብናል። ምክንያቱም፥ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና «ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች»[1] ሆኖአል። ከዚህም ከሞት ፍርድ እንዲድን የሚገባው አንድም የለም።

ነገር ግን በፍየል ደም ከዚያ ጥፋት የዳኑ እንደነበሩ እንደዚሁም የምንድንበት ከማንኛውም የእንስሳ ደም እጅግ የሚበልጥ ክቡር ደም ፈሶልናል። ይኸውም «የእግዚአብሔር በግ» የተባለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው።[2] እርሱም ለእኛ ሲል በእኛ ምትክ ተሰቅሎ ሕይወቱን ሰጠ። የእርሱም የእግዚአብሔር ልጅ ደም ከኃጢአት ሁሉ አንጽቶ ከፍርድና ከሙነኔ ሊያስጥለን ችሎታ አለው።

በጠፋችው ከተማ ውስጥ የዳኑት ሰዎች የሚድኑበትን ዘዴ በመስማት ብቻ ሳይሆን፥ የፍየሉን ደም በበር ላይ በመርጨት ዳኑ። እኛም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተልንና ክቡር ደሙ ከኃጢአትና ከፍርድ እንደሚያድነን ሰምተን ሳ ምንበት ብንቀር ደኅንነት የለንም። ዳሩ ግን እያንዳንዳችን የእግዚአብሔር ልጅ ወደደኝና ስለ እኔ ራሱን ሰጠ[3] ብለን በሙሉ ልባችን ብናምንበት ከኃጢአት ሁሉ በእርሱ ደም ተረጭተን እንድናለን፤ የፍርድና የኩነኔ መቅሠፍትም ከቶ አያገኘንም።[4]

አንባቢ ሆይ! በአንተ ምትክ ደሙን ባፈሰሰው መድኀኒ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነሃልን? በመስቀል ላይ በተረጨው ክቡር ደሙ ነጽተህ ድነሃልን? እስከ ዛሬ ድረስ ያለኸው ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ከሆነ፥ ዛሬ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ።»[5] የተባለው ቃል ለአንተም ሞምር ነው።

(1) ሮሜ 3፥23፡ 19፤ (2) ዮሐንስ 1፥29፤ 1 ጴጥሮስ 1፥19፤
(3) ገላትያ 2፥20፤ (4) ሮሜ 8፥1፤ (5) የሐዋርያት ሥራ 16፥31።

«የኰሎኔል ቃል አይለወጥም»

በወታደሮቹ መካከል አንዳንድ የማይታዘዙ ይገኙ ስለነበር አንድ ኰሎኔል ተቸግሮ ለወደፊት በደለኛውን በግርፋት ለመቅጣት አሳቡን ቈረጠ።

ከዕለታት አንድ ቀን ብዙ ሚላግዎች ተጥለውና ተበላሽተው ተገኙና ጥፋተኛ ግን እንደሆነ ምንም ባይገለጽ በየትኛው ድንኳን ውስጥ ያድር እንደነበረ በግልጽ ታወቀ። ኰሎኔሉ በዚያ ድንኳን ውስጥ የሚያድሩትን ሰዎች ሁሉ አሳሰረና ወደ እርሱ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ ምንም ቢመረምራቸው ጥፋተኛውን ለይቶ ለማወቅ አልቻለም። በመጨረሻም ኰሎኔሉ ነገሩን ቈርጦ «ከእናንተ አንድ ሰው ለጥፋተኛው የሚገባውን ቅጣት ለመቀበል ከመካከላችሁ ወጥቶ ወደ እኔ ቢመጣ የቀራችሁት ሁሉ ነፃ ትወጣላችሁ፤ ያለዚያ ግን ሁላችሁንም ማስገረፍ ይገባኛል» ብሎ ነገራቸው።

ኰሎኔሉ ይህን ሲናገር ሙሉ ጤና የሌለው አንድ ወጣት መለከት ነፊ በዚያ ድንኳን ውስጥ እንደሚያድር ረስቶ ነበርና ይህ ወጣት ከጓደኞቹ በስተኋላ በመቆሙ አይታይም ነበር። ቁርጥ የሆነው የፍርድ ቃል ከተነገረ በኋላ ግን ይህ ብላቴና ወደ ፊት ወጥቶ፥ «ጌታዬ ሆይ! እኔ የጥፋተኛውን ቅጣት ለመቀበል ዝግጁ ነኝ» አለው።

ኰሎኔሉ ይህን በሰማ ጊዜ ደንግጦ ብላቴናውን እያዘነ ከተመለከተው በኋላ ወደ ሌሎቹ ዘወር ብሎ በቍጣ ቃል፥ «ምነው እናንተ ሁላችሁ ፈሪዎች ናችሁ እንዴ? በመካከላችሁስ ወታደር መባል የሚገባው ሰው አይገኝምን? ይህ ብላቴና ጥፋተኛ እንዳይደለ ሁላችሁም ታውቃላችሁ፤ እርሱ ግን ስለ እናንተ ጥፋት ለመቀጣት ሲመጣ ዝም ትሉታላችሁን?» ብሎ ገሠጻቸው። ነገር ግን ሁሉ ዝም አሉ።

በዚህም ጊዜ ኰሎኔሉ እጅግ ተቸግሮ ግራ ገባው። ብዙ ጊዜም ነገሩን በልቡ ሲያወጣ ሲያወርድ ቈየና ብላቴውናን አይቶ ሊራራለት ሲፈልግ የተናገረውን የፍርዱን ቃል ደግሞ የግድ መፈጸም እንደሚገባው ተረዳ። በመጨረሻም በጣም እያዘነ ብላቴናው እንዲገረፍ አዘዘ።

ብላቴናው ሰውነቱ ምንም ደካማ ቢሆን የጀግንነት ልብ ነበረውና በሙሉ ፈቃዱ ግርፋቱን በድፍረት ይቀበል ጀመር። ነገር ግን ቅጣቱ ከማለቁ በፊት ብላቴናው እየደከመ መሄዱ በግልጽ ይታይ ነበርና በድንገት ከእስረኞቹ መካከል አንድ ሰው መጥቶ አለንጋውን ያዘና ከተወቀሰ ልብ በመነጨ በኀዘን ድምፅ ኰሎኔሉን፥ «ጌታዬ ሆይ! ጥፋተኛው እኔ ነኝና እኔ ልገረፍ እንጂ እርሱ አይገረፍ» ብሎ ብላቴናውን አቀፈው።

ብላቴናው ምንም ቢደክም ሰውዬውን በፈገግታ እየተመለከተ በሚቻለው ድምፅ፥ «የለም ወዳጄ ሆይ! የኰሎኔል ቃል አይለወጥምና ማንም አንተን ሊነካህ አይችልም» አለው።

በማግሥቱም ኰሎኔሉ ብላቴናው ይተኛበት ወደ ነበረው ወደ ሆስፒታሉ ድንኳን ሲሄድ ከሐኪሙ ጋር ተገናኝና፥ «ብላቴናው እንደምን ዋለ?» ብሎ ጠየቀው። ሐኪሙም፥ «የትላንትናው ቅጣት ከአቅሙ በላይ ስለነበረ እየደከመ ሄደ» ብሎ መለሰለት።

ኰሎኔሉም በጣም ደንግጦ ከሞት አፋፍ ላይ ወደ ደረሰው ብላቴና ቢሄድ በአልጋው አጠገብ ያ ጥፋተኛው ወታደር ተንበርክኮ ከእርሱ ጋር ሲነጋገር አገኘ። እነርሱ ግን ኰሎኔሉን አላዩትም ነበር።

በወታደሩ ግንባር ላይ የላብ ጠብታ ይታይ ነበርና በኀዘን ድምፅ፥ «ልጄ ሆይ! በምን ምክንያት ነው ይህን ያህል ያደረግኸው?» ብሎ እየደጋገመ ይጠይቀው ነበር።

የብላቴናው መልክ ምንም ቢመነምን በዓይኖቹ አንድ ታላቅ የደስታ ብርሃን ይታይ ነበርና፥ «በአንተ ፈንታ ቅጣቱን ለመቀበል የወደድሁበት ምክንያት ክርስቶስ አንተን ከኃጢአትህ ሊያድንህ ብሎ በአንተ ፈንታ በፍቅሩ እንደ ሞተልህ ምናልባት ለማስተዋል ይረዳሃል ብዬ ነው» ብሎ መለሰለት።

ወታደሩም፥ «እኔ እጅግ ጥፋተኛ ነኝና ክርስቶስ እኔን ምንም አይፈልገኝም» አለው።

ብላቴናውም፥ «ነገር ግን ክርስቶስ የመጣው በተለይ ስለ ኃጢአተኞች ነበረ፤ እርሱ ራሱም፥ «ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ለማዳን አልመጣሁም»[1] አለ። ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው፥ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤»[2] ወንድሜ ሆይ! ክርስቶስ ስለ አንተ ብሎ የከበረ ደሙን አፈሰሰ። የእርሱ ሞት ከንቱ ሆኖ ይቀራልን? አሁን እርሱ በልብህ ደጃፍ ቆሞ ሲያንኳኳ አትከፍትለትምን?[3] ብሎ ለመነው።

ብላቴናውም ይህን ሁሉ ከተናገረ በኋላ ድምፁ እየደከመ ሲሄድ በወታደሩ ራስ ላይ አኑሮት የነበረው እጁ ቀስ እያለ ይወርድ ጀመር። ያበሩ የነበሩት ዓይኖቹም እየተሰለመለሙ ይሄዱ ነበርና ከጥቂት ደቂቃ በኋላ የብላቴናው ነፍስ ወደ እግዚአብሔር ሄደች።

ይህ ታሪክ፥ ክርስቶስ፥ «ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም... በአፉ አልተገኘበትም፤ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤»[4] «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤»[5] የሚሉትን ጥቅሶች ያሳስባል።

(1) ማርቆስ 2፥17፤ (2) ኢሳይያስ 1፥18፤ (3) ራእይ 3፥2ሀ፤
(4) 1 ጴጥሮስ 2፥22፡ 24፤ (5) 1 ጴጥሮስ 3፥18።

ንጉሥ የማረው እስረኛ



በዱሮ ዘመን ወንጀል የሚሠሩ ዓመፀኞች ተይዘው ሲታሰሩ በግራና ቀኝ እጃቸው መቅዘፊያ ይዘው በጉልበታቸው ኃይል እየቀዘፉ የመንግሥትን መርከቦች በባሕር ላይ እንዲነዱ ይገደዱ ነበር።

አንድ ቀንም አንድ ንጉሥ፥ ክፉ ሥራ የሠሩ ወንጀለኞች ታስረው ወደሚገኙበት መርከብ ገባ። እስረኞቹም የታሰሩበትን ከባድ ሰንሰለት ሲመለከት እጅግ አዘነላቸው። በልቡም፥ «ከእነዚህ አንዱን ልፍታ» ሲል አሰበ።

መፈታት የሚገባውንም ለማግኘት፥ «አንተ! ወደዚህ የመጣህበት ምክንያት ምንድን ነው?» እያለ እያንዳንዱን እስረኛ ሲጠይቅና ሲመረምር፤ እያንዳንዳቸው እጅግ እያዘኑ፥ «ምንም ሳላጠፋና ሳልበድል፥ ክፉ ሰዎች ነገር ሠርተው ወደ ሹማምንት አደረሱኝ እንጂ ከተባለብኝ ነገር ንጹሕ ነኝ፤ ጌታዬ ሆይ! ምሕረት ያድርጉልኝ ከዚህም ስፍራ ያውጡኝ» እያሉ አጠንክረው ለመኑ።

ንጉሡም እያለፈ ሲመረምር ወደ አንድ ወጣት ጐበዝ ደረሰና፥ «አንተስ ምን አድርገህ ነው?» ቢለው ወጣቱ መልሶ፥ «ምሕረተኛ ጌታዬ ሆይ! እኔ እጅግ ክፉ አሽከር ነኝ፤ ለአባቴና ለእናቴ አልታዘዝም በማለት ብዙ ጊዜ ከበለልኩባቸው። እጅግ ክፉ ሥራም ሠራሁ፤ ሰረቅሁ፥ አታለልሁም፥ ያደረግሁትን ክፋት ሁሉ ዘርዝሬ ለመተረክ

እጅግ ብዙ ነው። የተገባኝን አግኝቻለሁ፤ ይህን ቅጣት ደስ እያለኝ እሸከማለሁ። ከዚህ ሺህ ጊዜ የሚበልጥ እንደሚገባኝ ተረድቻለሁ» ብሎ ኃጢአቱን ተናዘዘ።

ንጉሡ ግን እያንዳንዱ እስረኛ ለጥፋቱ የተገባውን ቅጣት እንደተቀበለ አረጋግጦ በቀልድ ሲዘልፋቸው፥ «እሪ! በእነዚህ ደጋግ ሰዎች መካከል ይህ ክፉ እንዴት ገባ! እነዚህን ደጎና ሰዎች እንዳያበላሽ ቢወጣ ይሻላል!» በማለት በክፉ ሥራው አፍሮ ለተናዘዘው ምሕረት አደረገለት። እርሱም ደስ ብሎት ሄደ።

የሠሩትን ኃጢአት ለመደበቅ ራሳቸውንም ለማጽደቅ የሚወዱ ሰዎች ዛሬም ቢሆን አይታጡም። ልባችንን የሚያውቅ አምላካችን ግን በቃሉ፥ «ንስሓ ግቡ»[1] በኃጢአታችሁም ተናዘዙ፥[2] «ክፉ ማድረግን ተዉ፥ መልካም መሥራትን ተማሩ»[3] ይለናልና የሚያጸድቀውን ምሕረት የሚያገኝ፥ ከልቡ፥ «እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ»[4] የሚል ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም፥ «ኃጢአትን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።»[5] ይላል።

(1) ማቴዎስ 4፥17፤ (2) 1 ዮሐንስ 1፥8-10፤
(3) ኢሳይያስ 1፥16-17፤ (4) ሉቃስ 18፥9-14፤ (5) ምሳሌ 28፥13።

ምነው ነቅተው ባመለጡ!

ሁለት መንገደኞች ደከማቸውና በባቡር ሐዲድ አቅራቢያ በሣር መካከል አረፍ እንዳሉ ወዲያውኑ አንቀላፉ። በዚያም ስፍራ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች፥ «ባቡር ሲመላለስ ከባቡሩ የሚፈናጠረው የእሳት ወላፈን በሣሩ ላይ ቢወድቅ ሣሩ ተያይዞ መንደራችን ሁሉ ይቃጠላል» በማለት በሣር መካከል መንገደኞች እንደተኙ ሳያውቁ ከበስተ ቤታቸው በኩል ሣሩን

አቃጠሉ። የእሳቱም ነበልባል በረታ፤ ወደየስፍራውም ሁሉ ደረሰ።

የዚህን አስፈሪ እሳት ኃይል ያልተገነዘቡ መንገደኞች በእንቅልፍ ወድቀው ሳሉ እሳቱ ከበባቸው፤ ልብሳቸውንም ይዞ ሰውነታቸውን ሲገርፍ ከተኙበት ባነኑ። አደጋ እንደ ደረሰባቸውም አስተውለው እየጮኹ ወዲያና ወዲህ ምንም ቢሮጡ በጣም ስለ ተጐዱ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሞቱ።



የሚያቃጥል እሳት ደርሶ እንደሚይዛቸውና እንደሚሞቱ ምንም ሳይጠረጥሩ በአንዲህ ያለ አደጋ መጐዳታቸውን ስታስብ አደጋው ሳይደርስባቸው በፊት ምነው ነቅተው ባመለጡ ኖሮ! ሳትል አትቀርም። ነገር ግን አንተ ራስህ በሥጋዊ ሳይሆን በነፍሳዊ እንቅልፍ ተይዘህ ከዚህ በባሰ፥ ግለት በገሃነመ እሳት እንዳትያዝ፥ ከሚመጣው ቁጣ ሽሹ![1] የሚለውን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ሰምተህ የእግዚአብሔርን ምሕረት እንድትፈልግ አሁን ንቃና ዳን!

«እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ብትል፥ «ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ ግቡ ተመለሱም።»[2] ስለ ኃጢአታችንም በተሰቀለው መድኅን «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ»[3] የሚለው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል የታመነና የተረጋገጠ ነው።

«አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል»[4] በማለት የተጻፈው ቃል የዚህን ታሪክ ፍሬ ነገር አጠቃልሎ ያሳያል።

(1) ማቴዎስ 3፥7፤ (2) የሐዋርያት ሥራ 3፥19-20፤
(3) የሐዋርያት ሥራ 16፥31፤ (4) ኤፌሶን 5፥14።

ከፈትለት!

አንዲት ድኃ ሴት ለቤት ኪራይ የምትከፍለው ገንዘብ ባጣች ጊዜ፥ የቤቱ ባለቤት መጥቶ ከቤቱ እንዳያስወጣት ስለ ፈራች ወደ ቤቱ አላስገባውም ብላ በሩን ቈለፈች። አንድ ቸር የሆነ ጐረቤትዋ ግን ችግርዋን ሰምቶ ለኪራይ የሚበቃውን ገንዘብ ሊሰጣት መጥቶ በሩን ቢያንኳኳ፥ «አዩ ጉድ! ባለቤቱ ይሆናል» ብላ ከፍርሃት የተነሣ ሳትከፍትለት ቀረች።

እኛ እግዚአብሔርን የበደልን ሰዎች ያለብንን ዕዳ የምንከፍልበት ምንም የለንም። ባለ ገንዘቡ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ መሥዋዕት ዕዳችንን ሁሉ ከፍሎልናልና እርሱ ወደ እኛ መጥቶ የልባችንን በር ያንኳኳል። እርሱን ተቀብለን ብናስገባው፥ «እኔ ሁሉን ከፈልሁልህ፥ አትፍራ» ብሎ ይቅር ይለናል። ነገር ግን ባንከፍትለትና እርሱ ራሱ ያመጣልንን ስጦታ ባንቀበል በፍርድ ቀን እርሱ ራሱ ፈራጅ ሆኖ፥ «እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ»[1] ብሎ በመፍረድ ከዘላለም ቤቱ ያሰናብተናል።

አንባቢ ሆይ! «እነሆ፥ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።»[2] የሚለውን የክርስቶስን ጥሪ ቸል አትበል።

(1) ማቴዎስ 7፥23፤ (2) ራእይ 3፥20።

«ዐሥር ሺህ ብር እሰጣለሁ»



ወደ አውስትራልያ የሚሄድ አንድ ትልቅ መርከብ በብዙ መቶ የሚቈጠሩ መንገደኞች ይዞ ሲሄድ ሳለ፥ በድንገት አደጋ አግኝቶት በሰጠመ ጊዜ ከሞት በተረፉት በጥቂት ሰዎች መካከል ከአደጋው ለመዳን በመፈለግዋ፥ አሥር ሺህ ብር ለመስጠት ስለፈለገች ስለ አንዲት ሴት ቀጥሎ ያለው ታሪክ ተነገረ።

አደጋም በሆነ ጊዜ ብዙ ሰዎች ታላቁን መርከብ ትተው በትንንሽ ታንኳዎች ገብተው አመለጡ። ሴቲቱም ከታንኳዎች ወደ አንዱ እንድትገባ በተጠራች ጊዜ ከፍርሃትዋ የተነሣ እምቢ አለች። በኋላ ግን ታንኳዎቹ ሁሉ ከሚሰጥመው ከትልቁ መርከብ ርቀው ስለነበር ምንም የመዳን ተስፋ አንዳልነበራትና ከሚሰጥሙት ጋር እንደምትሰጥም በተረዳች ጊዜ፥ በፍርሃትና በጭንቅ ተሞልታ በሚያሳዝን አኳኋን፥ «ብታስገቡኝ ዐሥር ሺህ ብር እሰጣለሁ።» ብላ ጮኸች። ዳሩ ግን ምንም በሚሊዮን የሚቈጠር ገንዘብ እሰጣለሁ ብትል በዚያች ሰዓት ዋጋ የለውም ነበር፤ ጊዜው አልፎ ነበርና። ወደ ታንኳ ግቢ በተባለች ጊዜ ጥሪውን ቸል ስላለች ሰጠመች።

አንባቢ ሆይ! እግዚአብሔር ከሚመጣው ቍጣ እንድትሸሽ ሲጠራህ ስማው እንጂ ቸል አትበለው። «እነሆ፥ የመዳን ቀን አሁን ነው።»[1] «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት፥ ... ልባችሁን አልከኛ አታድርጉ።»[2] ተብሎአል። ዛሬ ኃጢአትህን ትተህ

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብታምን ትድናለህ።[3] ነገር ግን «እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን?»[4] ተብሎ እንደተጻፈ፥ የእርሱን ጥሪ ቸል ብትል በኃጢአትህ ትጠፋለህ።

ሕይወትም እኔ ነኝ ብሎ ሲነግረን፥
ትንሣኤም እኔ ነኝ ብሎ ሲነግረን፥
ብርሃንም እኔ ነኝ ብሎ ሲነግረን፥
እንጀራም እኔ ነኝ ብሎ ሲነግረን፥
የሕይወት መጠጥም እኔ ነኝ ሲለን፥
መንገድም እኔ ነኝ ብሎ ሲነግረን፥
ከዚህ መንገድ ሌላ ብንገኝ ተላልፈን፥
ያውሬ እራት ነን እንጂ ሕይወትም አይኖረን።

(1) 2 ቆሮንቶስ 6፥2፤ (2) ዕብራውያን 3፥7-9፤
(3) የሐዋርያት ሥራ 16፥31፤ (4) ዕብራውያን 2፥3።

«ከእነርሱ ጋር መግባት እችላለሁ»

በአሳቡ ይቅርታ የማይገባኝ ነኝ እያለ ይጨነቅና ስለ ኃጢአቱ ይቸገር የነበረ አንድ ሰው ሕልም አለመ።

በዚህም ሕልም እርሱ ከሰማይ ደጅ ወደ ውጭ ቆሞ ሳለ አንድ ሠራዊት የሚሆኑ ሰዎች መጥተው የድል አድራጊነት መዝሙር እየዘመሩ ወደ ሰማይ ደጅ ሲገቡ አየ። በሰማይም ያሉት ሁሉ በደስታ አቀባበል ተቀበሉአቸው።

«እነዚህ እነማን ናቸው?» ብሎ መላእክትን ቢጠይቅ፥ እነርሱ «እነዚህ የነቢያት ወገን ናቸው» ብለው መለሱለት። ሰውዬው አዝኖ፥ «ምን ላድርግ? እኔ ከእነርሱ ወገን አይደለሁም። ከቶ ወደዚያ ለመግባት አልችልም» አለ።

ከዚያም በኋላ ነጭ ልብስ የለበሱ የድል አድራጊነት ደስታ የሚታይባቸው ሌሎች ሰዎች መጥተው ሲገቡ አየ።

«እነዚህስ እነማን ናቸው?» ብሎ ቢጠይቅ፥ መላእክቱ፥ «እነዚህ የሐዋርያት ወገን ናቸው» ብለው መለሱለት። ሰውዬውም እንደገና አዘኖ፥ «እኔ ከእነርሱ አይደለሁም። ከቶ ወደዚያ ለመግባት አልችልም» አለ።

እርሱ ግን በፍጹም ተስፋ ቈርጦ ለመሄድ አልቻለምና ገና በሰማይ ደጅ አጠገብ ሲጠብቅ ሳለ የሰማዕታት ሠራዊት የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው በደስታ ሲገቡ አየ። እርሱ ግን ከእነዚህ ጋር ደግሞ ሊገባ አልቻለም።

ከዚያ በኋላ ግን ከሌሎች ሁሉ እጅግ ትልቅ የሆነ ሠራዊት በልዩ ደስታ መዝሙር እየዘመረ ሲቀርብ አየ። በዚያም ሠራዊት ውስጥ ፊት ለፊት የሚገኙ ኃጢአተኛ የነበረችው ሴትና[1] በመስቀል የሞተው ወንበዴ[2] ነበሩ። በሠራዊቱ መካከል ምናሴ[3] የተባለና እንደ እርሱ የሆኑ ብዙ ሌሎች አየ። ሰውዬውም እነርሱ ሲገቡ የደስታ አቀባበል በጭራሽ አይደረግላቸውም ብሎ ሲያስብ ሳለ ሰማይ በሰባት እጥፍ በደስታ አቀባበል ጩኸትና እልልታ ተሞላ[4]።

መላእክቱም፥ «እነዚህ በታላቅ ጸጋ የዳኑ ታላላቅ ኃጢአት የሠሩ ሰዎች ናቸው» አሉት።

እርሱም፥ «እግዚአብሔር ይባረክ። እንግዲህ ከእነርሱ ጋር መግባት እችላለሁ» ብሎ ካመሰገነ በኋላ ከእንቅልፉ ነቃ።

የሰውዬው ሕልም፥ «ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቈጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ! ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ! ... ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ። እኔም፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት። አለኝም፦

እነዚህ ክታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ። ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ . . እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።»[5] የሚለውን የሐዋርያው ዮሐንስን ታላቅ ራእይ ያሰስባል።

ልባችሁ አይደንግጥ፤ እኔንም አምኑ፤
ብዙ ቦታ ሞልቶአል አብን ብትለምኑ።
ብዙ ቦታስ ባይኖር በላይኛው አገር
ከብዙ ቀን በፊት የለም ባልሁ ነበር።
እሰጣችኋላሁ ሰላሜን በብዙ፤
በደሜ ታጥባችሁ ጽድቅን እንድትገዙ።
ናፍቃችሁ እንደሆን ወደ አብ ለመሄድ
እኔ አለሁላችሁ ቀጥተኛው መንገድ።
ተመስገን ጌታችን ከዚህ ያደረሰኸን
ቀንበር ባርነትን ሰባብረህ ጣልህልን።

(1) ሉቃስ 7፥37-50፤ (2) ሉቃስ 23፥39-43፤ (3) 2 ዜና መዋዕል 33፥1-20፤ (4) ሉቃስ 15፥7፡10፡ 21-24፤ (5) ራእይ 7፥9-17።

የአንድ ሽማግሌ መንፈሳዊ ለውጥ

ብዙ ዓመት ታስሮ የኖረ አንድ ሽማግሌ ሰው በቅርብ ጊዜ ከእስር ቤት እንደሚፈታ ሰማ። ከወታደሮች አንዱ ክርስቲያን ስለሆነ ሽማግሌውን ለመርዳት አስቦ፥ «ከዚህ ስትወጣ የሚቀበሉህ ባልንጀሮች ታገኛለህን?» ብሎ ቢጠይቀው ሽማግሌው፥ «የለም» ብሎ መለሰለት።

«እንግዲህ ከዚህ ስትወጣ ምን ለማድረግ ታስባለህ?»

«ከአሥር ዓመት በፊት በሐሰት ከሶ ያሳሰረኝን ፖሊስ ፈልጌ እገድለዋለሁ።»

«ከዚያ በኋላስ?»

«እንደገና ተይዤ የሞት ፍርድ ይፈረድብኝና እሞታለሁ።»

«በኋላስ?»

«ገሃነመ እሳት። ነገር ግን ገሃነመ እሳት ስንኳ ከዚህ ካለፈው አሥር ዓመት የሚከፋ አይመስለኝም።»

ወታደሩ ይህን በሰማ ጊዜ፥ «መጽሐፍ ቅዱስ አለህን?» ብሎ ቢጠይቀው ሽማግሌው፥ «አዎን አለኝ» አለ።

«እንግዲህ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት አድርጎ እንደ ወደደ አንብበሃልን?»

«የለም አላነበብሁም። እግዚአብሔር ዓለምንና እንደ እኔ ያለውን ኃጢአተኛ ሁሉ ይጠላል እንጂ አይወድም» አለ።

ወታደሩም «የምጠይቅህን ነገር ስለ እኔ ብለህ ታደርገዋለህን? ብሎ ቢጠይቀው፥ ሽማግሌው፥ «አንተ ቸርነት አሳይተኸኛልና እሺ» አለ። ወታደሩም፥ «ዛሬ ማታ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ቁጥር 16ን አውጥተህ አንብብ» አለው።



በማግሥቱም የሽማግሌው መልክ ተለውጦ አዲስ ተስፋ እንዳገኘ በዓይኑ ይታይ ነበር። ወታደሩ፥ «አንብበኸዋልን?» ብሎ በጠየቀው ጊዜ ሽማግሌው፥ «አዎን፤ ብዙ ጊዜ እየደጋገምሁ አነበብሁትና ከደስታ ብዛት የተነሣ ተደንቄ አደርሁ። አሁን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

በእውነት መድኃኒቴ መሆኑን አምኜአለሁና አሳቤ ሁሉ ታድሶአል። አሁን ያን የከሰሰኝን ፖሊስ ለማግኘትና አቅፈው አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ እግዚአብሔር ዓለምን እንደወደደ ልነግረው አፈልጋለሁ እንጂ በምንም ልጉዳው አልፈልግም» ብሎ መለሰለት።

ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አርጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል»[1] ብሏል። ሐዋርያው ዮሐንስም፥ «ወዳጆች ሆይ፥ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ[2] ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል።»[2] በማለት የአሳብ መታደስ ወደ እርስ በርስ መዋደድ እንደሚመራ ጽፏል።

(1) 2 ቆሮንቶስ 5፥17፤ (2) 1 ዮሐንስ 4፥11።

የእኔ ውሳኔ

- እኔ በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ የተገባሁ ኃጢአተኛ መሆኔን ተረድቼአለሁ።

- ከዘላለም ጥፋት እንድድን፥ የዘላለምንም ሕይወት እንዳገኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍቅሩ የተነሣ የእኔን ኃጢአትና ፍርድ ተሸክሞ በእኔ ምትክ እንደሞተ አምኜ አመሰግነዋለሁ።

- ኃጢአቴን ተናዝዤና ትቼ፥ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቼ ራሴንና ሕይወቴን ሁሉ ለእርሱ አደራ ሰጥቼአለሁ፤ በሞቱም መሠረት ለዘላለም እንደሚጠብቀኝ አምናለሁ።

ይህን ውሳኔ ዛሬ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት አረጋግጫለሁ።

ስም .....

ቀን .....